ዓመታዊ የድጎማ ማለፊያ

በመጓጓዣ በኩል ያሉ ነፃነቶች እና እድሎች

የተሻሻለበት ቀን:
ኖቬምበር 1/ 2022

ደንበኞች የዓመታዊ የድጎማ ማለፊያቸውን በ King County Metro እና በ Sound Transit መጓጓዣዎች ላይ ያለምንም ክፍያ መጠቀም ይችላሉ:: የመጠቀሚያ ጊዜው ከአስራ ሁለት ወራት በኋላ ያበቃል::

ብቁነት

- የሚኖሩት ቦታ በ King፣ በ Pierce ወይም በ Snohomish ካውንቲመሆን አለበት::
- በአሁኑ ጊዜ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት የመንግስት የገንዘብ ድጎማ ፕሮግራሞች ውስጥ በላይ ተመዝግበዋል:

1. ለተቸገሩ ቤተሰቦች የሚያገለግል የጊዜያዊ እርዳታ (TANF)/ የግዛት ቤተሰብ እርዳታ (SFA) ፕሮግራም
2. የነፍሰ ጡር ሴቶች እርዳታ (PWA) ፕሮግራም (የWIC ወይም የእርግዝና ህክምናን አያካትትም)
3. የስደተኛ ገንዘብ እርዳታ (RCA) ፕሮግራም
4. ተጨማሪ የደህንነት ገቢ (SSI) ፕሮግራም (የማህበራዊ ዋስትና ገቢን አያካትትም)
5. አዛውንቶች ፣ ዓይነ ስውራን ወይም አካል ጉዳተኞች (ABD) ፕሮግራም
6. የመኖሪያ ቤት እና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች እርዳታ ፕሮግራም(HEN) (የቤቶች እና የከተማ ልማት (HUD) ን አያካትትም)

ከተቻለ፣ እባክዎን በስልክ ይመዝገቡ - በአካል መጥተው ለመመዝገብ ከፈለጉ የተወሰኑ ቀጠሮዎች አሉ:: በ Metro ማለፊያ ሽያጭ ቢሮ ውስጥ መመዝገብ አይችሉም::

ከዚህ በታች ካሉት ቢሮዎች ውስጥ አንዱ ላይ በመደወል ይመዝገቡ:

የህዝብ ጤና—የ Seattle እና King ካውንቲ የማህበረሰብ ጤና ተደራሽነት ፕሮግራም
800-756-5437
ከሰኞ እስከ አርብ: 8a.m.– 5p.m.
(1:00pm–2:00pm ዝግ ነው)

የማህበራዊ እና የጤና አገልግሎት መምሪያ (DSHS)
የደንበኞች አገልግሎት ማዕከል
877-501-2233
ከሰኞ እስከ አርብ:8a.m.– 5p.m.

የካቶሊክ ማህበረሰብ አገልግሎቶች (Catholic Community Services)
206-960-1582
ከሰኞ እስከ አርብ: 9 a.m.–4 p.m.

ከስድስቱ ብቁ የሆኑ የግዛት የገንዘብ ድጎማ ፕሮግራሞች ውስጥ **ለአንዱ ካልተመዘገቡ** ነገር ግን ብቁ ነኝ ብለው ካሰቡ፣ ለ DSHS የደንበኞች አገልግሎት ማእከል በ **877-501-2233** ላይ ይደውሉ::

ከዚህ በታች ካሉት ቢሮዎች ውስጥ አንዱን መርጠው በአካል ይመዝገቡ:

ORCA LIFT/የህዝብ ጤና ቢሮ
201 S Jackson St, Seattle, WA 98104
- ከሰኞ እስከ ሐሙስ: 8:30 a.m.–4:30 p.m. (ከ 1:00pm–2:00pm ዝግ ነው)
- አርብ: ቢሮ ዝግ ነው
- የወሩ ሁለተኛ እና አራተኛ ቅዳሜ: 10 a.m.–2 p.m. (በዓላት በሆኑ ቅዳሜና እሁድ በስተቀር)

Federal Way የህዝብ ጤና ሱቅ ፊት ለፊት
1640 S 318th Pl, Federal Way, WA 98003
- ከሰኞ እስከ ሐሙስ: 8:30 a.m.–5 p.m.
- አርብ: ቢሮ ዝግ ነው
- የወሩ የመጀመሪያ: ሶስተኛ እና አምስተኛ ቅዳሜ: 10 a.m.–2 p.m. (ከበዓላት ቅዳሜና እሁድ በስተቀር)

የካቶሊክ ማህበረሰብ አገልግሎቶች (Catholic Community Services)
Randolph Carter ማዕከል
100 23rd Ave S, Seattle, WA 98144
- ሰኞ እና አርብ: 9 a.m.–4 p.m.
- ረቡዕ: 9 a.m.–12 p.m.

ለበለጠ መረጃ
reducedfares@kingcounty.gov
206-477-4200
kingcounty.gov/SubsidizedAnnualPass

Amharic

King County METRO — Moving forward together | Sound Transit | Catholic Community Services — Serving people of all beliefs | Public Health — Seattle & King County | Washington State Department of Social & Health Services — Transforming lives